# ውሸት ሲያግት ዕውነት ሲነጥፍ

ውሸት ሲያግት ዕውነት ሲነጥፍ፣
ሐቅ ሲርቅ ሐሰት ሲገዝፍ፣
እንቶ ፋንቶ ታሪክ ሲዘርፍ።

የሚዋጋ የወያኔን ተረፍ መረፍ፣
የሚያቅራራ የሚፎክር የሚል ዘራፍ፣
ይገኝ ይሆን ከምድረ ዛፍ?

ቢበዛበት ቢፀናበት የበረዶ የውንሽፍር፣
ተከምሮ ቶቆልሎ ከዛፎች ስር
ጭቃ-መሳይ የበረዶ ድምር ጥምር፣
ለማራገፍ ቅጠላትን የዛፍን ዘር።

በምድር-ካሉ ከዕጽዋቱ ከዛፎች ዘር፣
በጽናቱ የሚነሳ በስመ ጥር፣
በማተቡ በእምነቱ ባሰረው ክር፣
ቢፈለግ ቢታሰስ በአገር ምድር፣
ለገዢዎች ለነጫጮች የሆነ ጠር፣
አልተገኘም እንደ ጽድ በዚህ አገር።

ምን ይሆን ምክንያቱ የጽድ ዘር ጽናቱ?
አልሞት ባይነቱ መኖሩ በዕምነቱ፣
ምን ይሆን ክልሆቱ የእምቢ ባይነቱ?
አለማጎብደዱ እጅ አለመንሳቱ፣
ምን ይሆን ብልሃቱ የታመቀ ዕውቀቱ?
ረግፈው ሲታዩ ሌሎቹ በወቅቱ፣
መኖሩ መግዘፉ በበጋ ክረምቱ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com